www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ጥር ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No. 10
ADDIS ABABA, 1st February, 2021

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻፹/፪ሺ፲፫
የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………………..……..ገጽ፲፪፱፻፵፯

**Content**

Regulation No. 480/2021
Ethio-Telecom Establishment (Amendment) Council of Ministers ………………….Page 12947

## ደንብ ቁጥር ፬፻፹/፪ሺ፲፫

## የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

ኢትዮ-ቴሌኮም የመንግስትን (የዲጂታል ፋይናንስ) አካታችነት ፖሊሲን ለማስፈፀም ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው በማመን፤

ይህንን በሚያስችል መልኩ የኢትዮ ቴሌኮም ማቋቋሚያ ደንብን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፭ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## REGULATION NO. 480/2021

## COUNCIL OF MINSTERS REGULATION TO AMEND THE REGULATION FOR THE ESTABLISHMENT OF ETHIO-TELECOM

**WHEREAS,** Ethio-Telecom have a vital role in the attainment of Government's Policy of digital finance inclusion;

**WHEREAS,** it is found important to amend Ethio- Telecom's Establishment Regulation;

**NOW, THEREFORE**, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No 1097/2018 and Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me



**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፹/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ማሻሻያ**

የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፯/፪ሺ፫ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪) እና (፯) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፩)፣ (፪) እና (፯) ተተክተዋል፤

"፭. **ዓላማ**

"፩/ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ለሕዝቡ መስጠትና ማዳረስ፤

፪/ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮም አገልግሎት መስጠት የሚችል በእውቀቱ፣ በችሎታው፣ በስራ ባህሉ ብቁና ተስማሚ የሆነ የሰው ኃይል መገንባት፤

፯/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ የንግድ ድርጅትን ማቋቋም ጨምሮ ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች ማከናወን፡፡"

፪/ በደንቡ ከአንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀፅ ፫ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፬) እና (፭) ተጨምረው፣ ነባሮቹ ንዑስ አንቀፆች እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀፅ (፮) እስከ (፱) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethio-Telecom Establishment (Amendment) Council of Ministers Regulation No. 480/2021"

**2. Amendment**

The Ethio-Telecom Establishment Council of Ministers Regulation No. 197/2011 is hereby amended as follows:

1/ Sub-Articles (1), (2) and (7) of Article 5 of the Regulation are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (1), (2) and (7) :

"5. **Purposes**

1/ to provide and make accessible up to date telecommunication technology service to the Public based on world class standard;

2/ to build competent work force with appropriate knowledge, skill, and work culture to provide world class telecom service;

7/ to engage in other related activities necessary for the attainment of its purpose including forming an entity."

2/ The following new Sub-Articles (4) and (5) are added after Sub-Article (3) of Article 5 of the Regulation and the existing subsequent Sub-Articles are re-numbered as from Sub-Article (6) up to (9), respectively :

www.chilot.me


"፬/ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎትና ተያያዥ ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ጠቅላላ አገላለጽ ሳይወሰን የቲኬት ክፍያን መፈፀም፣ የማናቸውም የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የቢል ክፍያን መፈፀም እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ የክፍያ ሰነዶችን አስመልክቶ በሚያወጣው ማንኛውም መመሪያ እና ማሻሻያ ላይ የሚፈቀዱትን አገልግሎቶች ማከናወን፤

፭/ በማናቸውም ኢንቨስትመንት በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ መሳተፍ፡፡"

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፮ ተተክቷል:-

"፮. **ካፒታል**

ለቴሌኮም የተፈቀደለት ካፒታል ብር አራት መቶ ቢሊዮን (፬፻ ቢሊዮን) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር አንድ መቶ ቢሊዮን (፩፻ ቢሊዮን) በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡"

፫. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

"4/ to engage in mobile money and related digital financial services. Without prejudice to the generality of the forgoing provision, provide the following services but not limited to m-ticketing, bill payment for any utilities and provide products services defined in any Payment Instrument Issuers Directive and its amendments issued by the National Bank of Ethiopia and amendment thereto;

5/ to participate in any equity investment domestically and at international level."

3/ Articles 6 of the regulation is deleted and replaced by the following new Articles 6:

"**6. Capital**

The Authorized Capital of the Telecom is Birr Four Hundred Billion (400,000,000,000) of which Birr One Hundred Billion (100,000,000,000) is paid up in cash and in kind."

**3. Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 1st day of February 2021.**

**ABIY AHMED (DR.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**